፬. ዙምራ በቤተሰቦቻቸውም ሆነ በአካባቢው ነዋሪ ሕብረተሰብ ዘንድ እንደ አፈንጋጭ ወይም እንደ እብድ ይቆጠሩ ነበር፡፡

፭. ምንባቡ በሶስት አንቀፆች የተደራጀ ነው፡፡

ተግባር ሁለት፡-

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡

፩. በ1964 ዓ.ም በተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ተቀባይነትን በማግኘቱ መተሳሰሪያውን ፍቅር ህይወቱንም ስራ በማድረግ የተመሰረተው ማህበረሰብ የቱ ነው?

ሀ. የአዊ ማህበረሰብ
ለ. የአውራምባ ማህበረሰብ
ሐ. አንፌሎ ማህበረሰብ
መ. የሳሆ ማህበረሰብ

፪. የምንባቡ አጠቃላይ ሀሳብ ምንድን ነው?

ሀ. የአቶ ዙምራን የህይወት ታሪክ መተረክ

ለ. የአውራምባ ማህበረሰብን ያታዊ አድልዎ ማመልከት

ሐ. የአውራምባ ማህበረሰብን የስራ ባህል ማስቀኘት

መ. ሁሉም መልስ ይሆናል፡፡

፫. ከሚከተሉት አንዱ የአውራምባ ማህበረሰብ ወንዶች የሚሰሩት ስራ አይደለም፡፡

ሀ. የእንጀራ መጋገር
ለ. ወጥ መስራት
ሐ. ጥጥ መፍተል
መ. መልስ የለም

፬. በምንባቡ ውስጥ የተገለፀው ማህበረሰብ መተሳሰሪያ ገመዱ ፍቅር መሆኑን የሚያስገነዝበው ስንተኛው አንቀፅ ነው

ሀ. አምስተኛው
ለ. ሁለተኛው
ሐ. ሶስተኛው
መ. አራተኛው

ሀ. ሱዳን ለ. ኢትዮጵያ ሐ. ኡጋንዳ መ. ታንዛንያ

፫. ከሚከተሉት ውስጥ የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ ተብሎ በዩኔስኮ የተመዘገበው የትኛው ነው?
ሀ. የመስቀል በአል ለ. የገዳ ስርዓት ሐ. ፍቼጨምበላላ
መ. ሁሉም

፬. ከኢትዮጵያ በዩኔስኮ የተመዘገቡ እና በብራና ላይ የተፃፉ የስነ ፅሁፍ ቅርሶች ስንት ናቸው?
ሀ. ስምንት ለ. ዘጠኝ
ሐ. ሰባት መ. አስራሁለት

፭. በዩኔስኮ የቅርስ መዝገብ የሚዳሰሱ ቅርሶች ተብለው ከተመዘገቡ የኢትዮጵያ ቅርሶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?
ሀ. አክሱም ለ. ላሊበላ ሐ. የጀጎል ግንብ
መ. መልስ አልተሰጠም

፮. ከሚከተሉት አንዱ በዩኔስኮ ከተመዘገቡ የስነ-ፅሁፍ ቅርሶች ውስጥ አይመደብም፡፡
ሀ. አፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዟ ንግሥት የፃፉት ደብዳቤ
ለ. ቀዳማዊ ኃይስላሴ ለአሜሪካው ፕሬዘዳንት የፃፉት ደብዳቤ
ሐ. ዳግማዊ አፄ ምንሊክ ለሞስኮው ንጉሥ የፃፉት ደብዳቡ
መ. ንጉሥ ሳህለሥላሴ ለእንግሊዟ ንግሥት የፃፉት ደብዳቤ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር፡-

ከዚህ በታች በቀረቡላችሁ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

፩. ባህላዊ ቅርስ ማለት ምን ማለት ነው?

፪. በባህላዊ ቅርስ ውስጥ የሚካተቱት ሀገር በቀል ቅርሶች ምን ምን ይመስሏችኋል?

፫. በቡሄ ጊዜ በሚደረደሩ ቃላዊ ግጥሞች ላይ በአብዛኛው ልዩነት እየታየ ያለው የት ነው?

ሀ. በገጠር　　　　ለ. በከተማ

ሐ. በትምህርት ቤት　　　　መ. በቀበሌ

## ተግባር ሦስት

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው መልስ ስጡ፡፡

1. በምንባቡ አንቀፅ ሁለት ላይ ቡሄ «ቀዳሚ የበዓላት መነሻ» ተብሎ የተገለፀው ለምንድን ነው?
2. የኔማ እመቤት ብትሰራ ዶሮ

   ሽታው ይጣራል ገመገም ዞሮ ሲል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?
3. በሁለቱ ትውልድ መካከል ያለው የባህል ውርርስ ላይ ልዩነት እንዲፈጠር ያደረገው ነገር ምንድ ነው?

## ተግባር አራት

**ማስታወሻ፡- ቅኔና የቅኔ አፈታት ዘዴዎች**

ቅኔ አዕምሮ እንዲቀለጥፍ፣ ጥልቅ የሆነ የማሰብ ችሎታ እንዲኖርና ነገሮችን በቀላሉ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚረዳ ጥበብ ነው፡፡ በተጨማሪም የሰው ልጅ ደስታውን ፣ሐዘኑን፣ ቁጭቱን ድጋፍ ተቃውሞውን ለመግለጽ ቅኔ ይቀኛል፡፡ በርካታ የቅኔ አይነቶች አሉ፡፡ የትኛውንም አይነት የቅኔ ዓይነት አዳምጠን ወርቁን (ሚስጥራዊ ፍቺውን) ለመረዳት ከሚያግዙ የአፈታት ዘዴዎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ ታሪክን ጠንቅቆ ማወቅ፣ ቃላትን ሁለት ቦታ በመክፈል፣ ቃልን በማጥበቅና በማላላት፣ ቃልን ከቃል በማጣመር፣ ከቃል ውስጥ ምዕላዶችን በማውጣት ፣ አንድ ቃል ከአንድ በላይ ፍቺ እንዳለው በመመርመር ወዘተ. የአንድን ቅኔ ሚስጥር ለመረዳት የሚያግዙ ዘዴዎች ናቸው፡፡

፬. ዶክተር ካትሪን ሀምሊን የየትሀገር ተወላጅ ናቸው?

፭. በምንባቡ ውስጥ በጎ ስራቸው የተዳሰሰላቸው ዶክተር የምን ሙያ ባለቤት ናቸው?

፮. ባለታሪኳ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆዩ ያስገደዳቸው ምክንያት ምንድን ነው?

፯. ምዶክተር ካትሪን ሀምሊን የመጀመሪያውን የፌስቱላ ሆስፒታልያ ያሠሩት የት ነው?

፰. ዶክተር ካትሪን ሀምሊን ሴቶችን በህክምና ከመርዳት ባለፈ ምን ምን ጉዳዮች ያከናውኑ ነበር?

፱. የዶክተሯ አስተዋፅኦ በዋጋ የሚተመን ይመስላችኋል? እንዴት?

፲. የበጎ ስራ ባለቤት ለሆኑት ዶክተር ሀምሊን ከተበረከቱላቸው ሽልማቶች መካከል ቢያንስ ሶስቱን ዘርዝሩ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ጭውውት

ጭውውት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በዕርስ የሚያካሂዱት ምልልስ ነው፡፡ በጭውውት ወቅት አንዱ ከሌላው የችግርን መፍቻ ሀሳብ ያገኝበታል፤ ልምድም ይጋራበታል፡፡ በጭውውት ጊዜ የእርስ በዕርስ መደማመጥና መከባበር እንደተጠበቀ ሆኖ ቀልዶችን ጣል ጣል እያደረጉ ዘና ማለት የተለመደ ነው፡፡

### ተግባር አንድ፡-

አራት አራት ሆናችሁ በመቧደን ከዚህ በታች የቀረበላችሁን ጭውውት በተግባር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

(እናት ወ/ሮ ትዕግስት እርጅና የተጫጫናቸው ከመሆናቸውም በላይ፣ አብዛኛዎቹ ጥርሶቻቸው ወልቀው ከቀሩት ጥቂት ጥርሶች መካከል የመንጋጋ ጥርሳቸውን አሟቸዋል፡፡ ዛሬ ደግሞ የሆስፒታል ቀጠሮ አላቸው፡፡ ልጃቸው ይበልጣል ባለቤቱን አመለወርቅን ወደ እናቱ ቤት ልኮ ሀኪም ቤት የሚወስዳቸውን መኪና ለማፈላለግ ወደኋላ ቀርቷል፡፡ አመለወርቅ አማቷ ቤት በደረሰች ጊዜ ወ/ሮ ትዕግስት ፊት ለፊት ተቀምጠው

1.2.1. ከሲጋራ

1.2.2. ከጫት

1.2.3. ከአልኮል መጠጥ

ተግባር አንድ፡-

«የሰብአዊ እሴቶች ጥቅም» በሚል ርዕስ ሶስት አንቀጽ ያለው ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችል ቢጋር አዘጋጁ፡፡

ተግባር ሁለት፡-

በተግባር አንድ ያዘጋጃችሁትን ቢጋር መሰረት አድርጋችሁ ሶስት አንቀጽ ያለው ድርሰት ጻፉ

ተግባር ሶስት፡-

ጉርብትና የሚለውን ምንባብ ካነበባችሁት በኋላ ከአካባቢያችሁ ማህበራዊ ትስስር ጋር በማነፃፀር አራት አንቀፅ ያለው ድርሰት ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

**ድርብ ቃላት**

ድርብ ቃል ሁለት የተለያየ ትርጉም ያላቸው ቃላት በአንድ ላይ ሆነው አንድ ለየት ያለ ትርጉም የሚያስገኙበት የቃላት ቅንጅት ነው፡፡ ድርብ ቃል በሰረዝ ወይም ያለሰረዝ ቃላትን በማዋሀድ ሊፃፍ ይችላል፡፡

ምሳሌ፡- ዕኩለ ሌሊት


ቤተ-መዘክር

ተግባር አንድ፡-

በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉ ድርብ ቃላትን ተጠቅማችሁ ከታች ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

# የህይወት ቅዳጆች



**ቅድመ ማዳመጥ**

፩. በህይወታችሁ የማትረሱት አሳዛኝ ገጠመኝ ካለ እስኪ ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው?

፪. ‹‹የህይወት ቅዳጆች›› በሚል ርዕስ ስር ምን ምን ጉዳዮች የሚዳሰሱ ይመስላችኋል?

## አዳምጦ መረዳት

ያዳመጣችሁትን ጹሁፍ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመምረጥ መልሱ፡፡

፩ በምንባብ ውስጥ እንባው አንዴ እየጠቆረና እየወፈረ፣ሌላጊዜ እየቀጠነና ውሃ እየመሰለ ክረምት ከበጋ ግቢውን አቋርጦ ይፈሳል የተባለው ምንድን ነው?

ሀ. የቧንቧ ውሃ ለ. የአካባው ወንዝ

ሐ. የመጸዳጃ ቤቱ ፍስሽ መ. የሚወርደው ጎርፍ

- ✓ የአድማጭን ማንነት መለየት
- ✓ ንግግር በሚደረግበት ርዕስ ላይ ሰፋ ያለ መረጃ ማሰባሰብ
- ✓ መረጃን የሚያመለክት ሀሳብ በአስተዋፅኦ መልክ ማዘጋጀት
- ✓ በመድረክ ላይ የሚቀርበውን ንግግር እንዴት እንደሚቀርብ መለማመድ

ለ. የንግግር አቀራረብ

- ✓ አድማጮችን በሚያረካ መንገድ ንግግር ማድረግ
- ✓ ንግግር በማቅረብ ሂደት ውስጥ የአድማጮችን ሁኔታ በመከታተልና የንግግሩ ሀሳብም ሆነ አቀራረብ ማራኪ እንዲሆን ማድረግ
- ✓ በንግግሩ ማቅረብ ሂደት መግቢያ እና ዝርዝር ሐሳብ እንዴት ያለ አቀራረብ ሊኖረው እንደሚገባ አስታውሶ መተግበር፡፡

ተግባር አንድ፡-

የአጭር ልቦለድ አላባውያን በተመለከተ አምስት አባላት ያለው ቡድን በመመስረት መመሪያ እየተሰጣጣችሁ የቃል ንግግር አድርጉ፡፡

ተግባር ሁለት፡-

“እውቀት ለመለወጥ” በሚል ርዕስ በየተራ እየወጣችሁ ክፍል ውስጥ የቃል ንግግር አድርጉ፡፡

ተግባር ሶስት፡-

ከዚህ ቀደም ካነበባችሁት ልቦለድ ታሪክ ወይም በሬዲዮና በቴሌቪዥን ከሰማችሁት ትረካ ውስጥ የምታስታውሱትን በየተራ እየወጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው፡፡

፮. ሀብቷ ቀና

ሀ. እድለኛ ሆነች　　ለ. ለጋብቻ ታጨች

ሐ. ሀብታም ሆነች　　መ. ገንዘብ አገኘች

፯. ጥራዝ ነጠቅ

ሀ. ግልብ እውቀት ያለው　　ለ. ብዙ ያልተማረ

ሐ. ጥልቅ ትምህርት የሌለው　　መ. ሁሉም

፰. የአዞ እንባ

ሀ. የለበጣ ሀዘን　　ለ. እውነተኛ ሀዘን

ሐ. መከፋት　　መ. ማልቀስ

፱. አይነ ልም

ሀ. ቆንጆ　　ለ. ምቀኛ

ሐ. ተንኮለኛ　　መ. የዋህ

፲. አገም ጠቀም

ሀ. ሁሉን መጥቀም　　ለ. ያዝ ለቀቅ

ሐ. ዓይን አፋር　　መ. ሄድ መጣ

ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

> መሸጋገሪያ፣ቃላት ሐረጋት
>
> የሀሳብ ተመሳሳይነት ያላቸውን ዓረፍተ ነገሮችና አንቀፆች በማያያዝ እንደድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ቃል ወይም ሀረግ ነው፡፡ ከነዚህ ቃላትና ሀረጋት መካከልም የተወሰኑት፡-

-ተውሳከ ግስ ከሆነ-----ሀረጉ ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ
-መስተዋድድ ከሆነ----ሀረጉ መስተዋድዳዊ ሐረግ
ይሆናል።

ምሳሌ፡-የብር ቀለበት-----ስማያዊ ሐርግ
-እጅግ በጣም ጎበዝ ------ቅፅላዊ ሐረግ
-በድንገት መጣ።----ግሳዊ ሐረግ
-ልጁ ክፉኛ---------ተውሳከግሳዊ ሐረግ

- ✓ መስተዋድዳዊ ሀረግ ቀኝ መሪም ግራ መሪም መሆን ይችላል።

ምሳሌ፡- ወደ ቤት---መ.ሐ
-ከልጁ ጋር----መ.ሐ

ተግባር አንድ፡-

በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ሐረጎች አይነት በምሳሌው መሰረት ጥቀሱ።

ምሳሌ፡-

ዘይነባ አክስቷን ለመጠየቅ ወደ ደሴ ሄደች።

- ➢ ወደ ደሴ-----------መስተዋድዳዊ ሐረግ

ሁሉን ነገር በሆዱ የሚይዝ ሰው እራሱን ይጎዳል።

- ➢ ሁሉን ነገር በሆዱ የሚይዝ ሰው---------ስማዊ ሐረግ

፩. ልጁ ወደሆስፒታል ተወሰደ።

፪. ወይኒቱ በጣም ጎበዝ ተማሪ ናት።

፫. የፈራረሱ ቤቶች በአዲስ መልክ እንደገና ተሰሩ።

፬. ትናንት የታመመው ተማሪ ተሻለው።

፭. ሄኖክ የእግር ኳስ ለመመልከት ስቴድየም ገባ።

ተግባር ሁለት፡-

የተለያዩ የሀረግ አይነቶችን ተጠቅማችሁ አምስት አረፍተ ነገር መስርቱ።

፩. በምንባቡ አንቀፅ ሁለት ላይ በአገራችን ለሚታዩ ውስብስብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምክንያት ተብሎ የተጠቀሰው ምንድን ነው?

ሀ. የህዝብ ቁጥር እድገት　　ለ. የልማት ፖሊሲ

ሐ. የውልደት ምጣኔ　　መ. የሀብት ብክነት

፪. በምንባቡ መሰረት የኢትዮጵያ መንግስት ያወጣው ፖሊሲ የትኛው ነው?

ሀ. የትምህርት ፖሊሲ　　ለ. የጤና ፖሊሲ

ሐ. የሥነሕዝብ ፖሊሲ　　መ. የግብርና ፖሊሲ

፫. የኢትዮጵያ የስነሕዝብ 70 በመቶ ወጣትና ሠርቶ ያልደከመ መሆኑ የተገለፀው መየትኛው አንቀፅ ነው?

ሀ. በአንቀፅ አንድ　　ለ. በአንቀፅ ሁለት

ሐ. በአንቀፅ አራት　　መ. በአንቀፅ ሶስት

፬. በአንቀፅ ሶስት ላይ የአገር እድገት ወሳኝ ግብዓት ይሆናል ተብሎ የተገለፀው በምን የጎለበተ ህዝብ ነው?

ሀ. በዕውቀት　　ለ. በአመለካከት　　ሐ. በክህሎት　　መ. ሁሉም

፭. ዘላቂ እና አስተማማኝ ሊሆን አይችም የተባለው ምንን ከግምት ያላስገባ የሥነሕዝብ ሁኔታ ነው።

ሀ. ጥረት　　ለ. ውልደት　　ሐ. ልማት　　መ. ብዛት

## ተግባር ሶስት፡-

በምሳሌው መሰረት ከምንባቡ የምክንያትና ውጤት ትስስር ያላቸውን አምስት ዓረፍተ ነገሮች አውጥታችሁ አመልክቱ።

ምሳሌ:- ያልተጣጣመ ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት መኖር ምክንያቱ ከፍተኛ የውልደት ምጣኔ ነው።

ምክንያት:- ያልተጣጣመ ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት

ውጤት:- ከፍተኛ የውልደት ምጣኔ

## ክፍል ሶስት:- ጽሕፈት

### ተራኪ ድርሰት

በጣም ከተለመዱት አራት ዋና ዋና የድርሰት አይነቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን በጊዜ ቅደም ተከተል ስላለፈ ድርጊት የሚተረክ ወይም የሚያትት ጹሁፍ ተራኪ ድርሰት ተብሎ ይጠራል። ተራኪ ድርሰት የሁነቶችን የድርጊት ቅደም ተከተል ጠብቆ እንዲህ ሆነ፣ እንዲህ ተደረገ---እያለ የሚተርክ ጹሁፍ ነው። ታሪኩን የሚነግረን እራሱ የድርጊቱ ተካፋይ ወይም ተመልካች ሊሆን ይችላል።

ምሳሌ:- አቶ ፍቅር ከአባታቸው ከአቶ ይበልጣል አጥናፉ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ማህደር በላይ አዲስ አበባ ከተማ ታህሳስ 12/1984 ዓ.ም ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለአቅመ ትምህርት ሲደርስ በአካባቢያቸው ከሚገኘው እውቀት ፋና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርታቸውን ተከታተሉ። ከዚያም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በፍኖተ ጥበብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተምረዋል።

#### ተግባር አንድ:-

የአንድን የምታውቁት ታዋቂ ሰው የሕይወት ታሪክ በአምስት አንቀፅ ፃፉ።

#### ተግባር ሁለት:-

የራሳችሁን የሕይወት ታሪክ በሶስት አንቀፅ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

**ተግባር፡-**

የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቾ በሰንጠረዡ ውስጥ በቀረበው ምሳሌ መሰረት አስቀምጡ፡፡

| ቃል | እማሬያዊ ፍቾ | ፍካሬያዊ ፍቾ |
|---|---|---|
| ንብ | ማር አምራች በራሪ ፍጡር | ታታሪ፣ ትጉህ፣ ሰራተኛ |
| ዱባ | | |
| ቋንጣ | | |
| አንበሳ | | |
| ተልባ | | |
| እንጀራ | | |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

**ገቢርና ተገብሮ ግሶች**

ገቢር ግሶች፡- አንድ ሰው የሚፈፅመውን ድርጊት ወይም ተግባር የሚገልፁ ናቸው፡፡ አምዱ ምንም አይነት ቅጥያ የማይጨመርበት ሲሆን የተፈፀመ ድርጊትን የሚጠቁም በመሆኑ ሃላፊ አምድ ነው፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

# የምድራችን ጀግና




(ዶ/ር ተወልደብርሀን ገ/እግዜአብሔር)

**ቅድመ ማዳመጥ**

፩. በርሃማነት ማለት ምን ማለት ይመስላቸዋል?
፪. እፅዋትንና የሰውን ልጅ ሕይወት የሚያገናኛቸው ምን ይመስላችኋል?
፫. ዶክተር ተወልደ ብርሃን ገብረ እግዚአብሔር ማን ናቸው?

### አዳምጠ መረዳት

### ተግባር አንድ፡-

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡

ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የቃላት ተቃራኒን ምንነት ተረድተን ቃላትን ከተቃራኒዎቻቸው ጋር አዛምደናል፡፡ በመቀጠልም ዓረፍተ ነገር ከአገልግሎት አንፃር ጥያቄያዊ፣ ትዕዛዛዊ፣ ሀተታዊ እና አጋናኝ ተብሎ እንደሚከፈል አስታውሰን ዓረፍተነገሮችን ከአገልግሎታቸው ጋር ለማዛመድ ችለናል፡፡

በአዎንታዊ ወይም በዓሉታዊ መልክ የሚቀርብ ዓረፍተ ነገር ሀተታዊ ዓረፍነ ነገር ሲባል ትዕዛዝን ለማመልከት የምንጠቀምበት ዓረፍተነገር ደግሞ ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገር እንደሚባል አይተናል፡፡ በተጨማሪም መጠይቃዊ ቃላትን በተዋቃሪነት የያዘ ዓረፍተነገር ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር ሲባል ነገሮችን አግዝፎ ወይም አሳንሶ ለማቅረብ የሚያገለግል ዓረፍተነገር አጋናኝ ዓረፍተነገር እንደሚባል ተገንዝበናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

### ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ፃፉ፡፡

፩. እንጀራ ወጣለት

፪. የውሀ ሽታ

፫. የግንባር ስጋ

፬. ገመና ከታች

፭. ጉልበተ አወጣ

፮. ደግ ዋለለት

### ተግባር ሁለት፡-

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ሐተታዊ (አዎንታዊ፣ አሉታዊ)፣

፰. “ጉንጭ ማልፋት ቢሆንም ቅሉ” ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል?

ሀ. ከንቱ ልፋት　　　ለ. ጉንጭ ማሸት

ሐ. ስኬታማ ጥረት　　　መ. ጉንጭ መምታት

፱. ለሰላም መታሰቢያነት በአገራት ባንዲራ ጎን የሚቀረፀው የምን ምስል ነው?

ሀ. የግመል　　ለ. የዕርግብ　　ሐ. የአንበሳ　　መ. የንስር

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር፡-

በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያታችሁ ከስምምነት ላይ የደረሳችሁበትን ሀሳብ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፩. ሰላም ምንድን ነው?

፪. የሰላም መኖር ለእድገት ያለውን አስተዋፅኦ እንዴት ትገልፁታላችሁ?

፫. ሰላምን ማስጠበቅ የማን ሀላፊነት ይመስላችኋል?

፬. በአንድ ሐገር ሰላም ከሌለ ተጎጅዎች እነማን ይመስሏችኋል?

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### ሰላም ለዕድገታችን

**ቅድመ ንባብ**

፩. ለሰላም እጦት ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችን ዘርዝሩ፡፡

፪. የሰላም ዕጦት በአንድ ሀገር ላይ ምን አይነት ጉዳት ያለው ይመስላችኋል?

፫. ከዚህ በታች ያለውን ስዕል አይታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ግለፁ፡፡

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ “እውነት” ስህተት ከሆኑ ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡

፩. የአንድ ሀገር እድገት የሚረጋገጠው ሰላም ሲኖር ብቻ ነው፡፡
፪. ሁልጊዜም ሰላም ሊገኝ የሚችለው ተመራማሪዎች በሚያደርጉት ጥናትና ምርምር ነው፡፡
፫. ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየት የሕዝብ ምኞት ነው፡፡
፬. አስተማማኝ ሰላም ዘላቂነት ያለውና በሕዝብ በጎ ፈቃደ ሊፈጠር የሚችል አይደለም፡፡
፭. ጦርነት ሁልጊዜ አስከፊ ገፅታ ነው ያለው ማለት አይቻልም፡፡
፮. በሀገራት መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ከህዝብ መጠላላት የመነጩ አይደሉም የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡
፯. ማንኛውም ሕዝብ ጦርነትን አይደግፍም፡፡
፰. ጦርነት ባለበት ዲሞክራሲ፣ ዲሞክራሲ ባለበት ጦርነት አይታሰብም፡፡
፱. ከሰላም የተሻለ ኑሮ ሲገኝ፤ ከጦርነት ግን የሚገኘው እልቂት፣ ፍጅት፣ ረሀብና እርዛት ነው፡፡
፲. “ጦርነትን ለማስወገድ ለጦርነት ጀሮህን አትስጥ” የሚለው አባባል ትክክል ይመስላል፡፡

፯. በምንባቡ አንቀፅ አራት ላይ "ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየት" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. ከአድልዎ የፀዳች

ለ. በዕድገት ያዘገመች

ሐ. በድህነት የተራቀቀች

መ. በቴክኖሎጂ የበለፀገች

፰. በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?

ሀ. ጦርነት ለሀገር እድገት ወሳኝ መሆኑን

ለ. ሰላም ለሀገር ብልፅግና የማይተካ ሚና ያለው መሆኑን

ሐ. ያለጦርነት ሰላም ሊሰፍን የማይችል መሆኑን

መ. ጦርነት ከሰላም የሚመነጭ መሆኑን

## ተግባር ሶስት

"ሰላም" በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም በደንብ አንብቡና መልዕክቱን በአንድ አንቀፅ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ሰላም

አንዱ ለፀሎተ ውዳሴው፤
ሌላው ለፍሬ ከርስኪ ጉባዔው፤
ደሞ ሌላው ... ለነገር ማጣፈጫ፤
ለፈራጅ አዕምሮ መቀጣጫ፤
ለአምባ-ገነን ሥልጣን መጨበጫ፤
ስንቱ ለከንቱ በከንቱ ያነሳሻል፤
አንስቶ .... ክቦ ... ክቦ ... ይጥልሻል።

ከልጅነቴ ጀምሮ የምሰማት፤
ልጅ፣ ሽማግሌው የሚወዳት፤
የማትለወጥ ጣፋጭ ቃል፤

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ዓረፍተ ነገር

በውስጣቸው ከሚይዙት የግስ ብዛት አንፃር በሁለት ይከፈላሉ፡፡

፩. ነጠላ ዓረፍተ ነገር፡- አንድ ግስ ብቻ ያለው ዓ.ነገር ነጠላ ዓ.ነገር ተብሎ ይጠራል፡፡

ምሳሌ፡- አልማዝ ጫማና ቦርሳ ገዛች፡፡
ህፃን ልጅ ወተት ይወዳል፡፡
ልጁ መጣ፡፡

፪. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር፡- ከአንድ በላይ ግስ ያለው ዓ.ነገር ውስብስብ ዓ.ነገር ይባላል፡፡

ምሳሌ፡- ቀለሙ እያወራ ይበላል፡፡
ሜላት ስለምትፈራ ችግሯን አትናገርም፡፡
ፈትያ ወንደሟ ወደውጭ ሀገር ስለሄደ አዘነች፡፡

### ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር በማለት ለዩ፡፡

፩. አብዱ ዛሬ ብዙ ጥያቄ አቀረበልኝ፡፡
፪. ጨዋታውን ፊት ለፊት በማየቴ ደስ አለኝ፡፡
፫. ዳናዊት እስር ቤት ሄዳ እህቷን ጠየቀች፡፡
፬. ቀለሙ ፊቱን ታጠበና ቁርሱን በላ፡፡
፭. አቤል ቁልፍ ወስዶ በሩን ከፈተ፡፡
፮. እውቀት ከጥበብ ጋር ቤተመፃሕፍት ሄደች፡፡
፯. አቤኔዘር የክፍል ስራውን ሰርቶ አሳረመ፡፡
፰. ወንድሙ ከመኝታው ተነስቶ አልጋ አነጠፈ፡፡
፱. የያፌት ወንድም ቁምሳጥኑን ከፈተ፡፡
፲. ፍቅር ዛሬ ጠዋት ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

፬. እንደ ጽሑፉ ገለፃ ከሆነ እየተከሰተ ላለው የአፈር መሸርሸር አደጋ
ዋና ምክንያቱ ------------------------- ነው፡፡
ሀ. አውሎ ነፋስ ሐ. ወራጅ ውሃ
ለ. ለም አፈር መ. ሀ ና ሐ መልስ ናቸው
፭. በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በቆላማውም ሆነ በደጋማው የሀገራችን ክፍል ችግር እየፈጠሩ ካሉ በሽታዎች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?
ሀ. ወባ ለ. ጋንዲ ሐ. ኤች አይቪ መ. ሁሉም
፮. ከሚከተሉት አንዱ ለበርካታ ዓመታት የተመዘገበን የአየር ንብረት መቀየር የሚመለከት ነው?
ሀ. የአየር ሁኔታ ለ. የአየር ንብረት ለውጥ
ሐ. የአየር ንብረት መ. የዝናብ መጠን
፯. የኢትዮጵያ ታላላቅ ወንዞችና ጅረቶች መነሻቸው ከየት ነው?
ሀ. ከደጋ ለ. ከበርሀ ሐ. ከቆላ መ. ከአባይ
፰. «የአባይን ልጅ ውሀ ጠማው» ከሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር በፍች ተመሳሳይ የሆነው የትኛው ነው?
ሀ. የተኳኸን ልጅ ውሀ ወሰደው፡፡
ለ. የባሮን ወንዝ አውሬ ጠጣው፡፡
ሐ. የላጭን ልጅ ቅማል በላው፡፡
መ. የድመትን ልጅ ውሻ በላው፡፡
፱. የዚህ ምንባብ አብይ መልዕክት ምንድን ነው?
ሀ. በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በዓለም ላይ የተለያዩ ችግሮች እየተከሰቱ መሆኑን ማሳየት
ለ. ለአየር ንብረት ለውጥ ግንባር ቀደም ተዋናዮቹ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት መሆናቸውን ማስረዳት
ሐ. የበለፀጉ ሀገራት በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ምንም ዓይነት አስተዋፅዖ እንደማያደርጉ ማተት እንደሚፈስ መግለፅ

መ. ውሀ ከደጋማው ቦታ በመነሳት ወደ በርሃማው ቦታ

## ተግባር ሶስት

ግጥሙን በጥሞና አንብቡና ከታች የቀረበላችሁን ጥያቄዎች ትክክለኛ ውን መልስ በመምረጥ መልሱ

### ይኸው እንደ ዋዛ

ይኸው እንደዋዛ!
ተራሮች ፈለሱ
ኮረብታዎች ተወሰዱ
ውሆች ተሰደዱ
ማነን? ብንላቸው
ፈጽመው ረሱን
በ'ኛ ተሰይመው
ዛሬ 'ኛን' ስም ነሱን፡፡
ይኸው እንደዋዛ!
ባለበት እንዲገኝ
መሬት መች ታመነ
መሀል የነበረው
ዳርቻችን ኾነ፡፡
ይኸው እንደዋዛ!
አራሹ ሳይለግም
ሳይሳሳ ደመና
ህላዌን ድርቅ መታት
ዘር መውደቂያ አጣና፡፡

(በዕውቀቱ ስዩም፣ 2001 ዓ.ም፣ ስብስብ ግጥሞች)

፩. ግጥሙ ባለስንት አርኬ ነው?

ሀ. ሁለት ለ. ሶስት ሐ. ዘጠኝ መ. አስራ ስምንት

፪. በግጥሙ የመጀመሪያው አርኬ ላይ "ማነን? ብንላቸው ፊፅመው ረሱን" የተባሉት እነማን ናቸው?

ሀ. ተራሮች　　ለ. ውሀዎች　　ሐ. ኮረብታዎች

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

፫. በግጥሙ መሰረት መሬት ያልታመነው በምንድን ነው?

ሀ. እህል ባለመቀበል　　ለ. ቤት መስርያ ባለመሆን

ሐ. ባለበት ባለመገኘት　　መ. መዝናኛ ባለመሆን

፬. ከሚከተሉት አንዱ አማርኛ ቋንቋ ከግዕዝ የተዋሰው ቃል ነው፡፡

ሀ. ህላዌ　　ለ. አጣና　　ሐ. ሳይሳሳ　　መ. ዳርቻ

፭. በግጥሙ መሰረት ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ገበሬዎች እርሻቸውን እያረሱ ነው፡፡

ለ. ሰማይ ዝናብ መስጠቱን አቁሟል፡፡

ሐ. መሬት ባለበት እየቀጠለ አይደለም፡፡


መ. የሰው ልጅ በርሃብና በችግር እየተመታ ነው፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ተግባር፡-

፩. በክፍል ሶስት ላይ የቀረበውን ስዕል ከዚህ በታች ከቀረበው ጋር በማነጻጸር ጥልቅ የሆነ ትንታኔ በጽሁፍ ስጡ፡፡

፪. የጻፋችሁትን ጥልቅ ማብራሪያ እርስ በዕርስ በመቀያየር እርማት ተሰጣጡ፡፡



ተግባር ሶስት

በ‹‹ሀ›› ስር የቀረቡትን ያልተለመዱ ቃላት በ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት ፍችዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. ሐኬት | ሀ. መንቀጥቀጥ |
| ፪. ገርበብ | ለ. መከልከል |
| ፫. ስርቅታ | ሐ. መባከን |
| ፬. ማሞናደል | መ. ማቃጠል |
| ፭. መክላት | ሠ. ክፋት |
| ፮. ቅራተኛ | ረ. ከፈት |
| ፯. መዋተት | ሰ. ከብት ጠባቂ |
| ፰. መፋጀት | ሸ. ማቀማጠል |
| | ቀ. ህቅታ |
| | በ. ማስወገድ |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

ተግባር፡

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ ወይም ውስብስብ ዓርፍተ ነገር በማለት ለዩ፡፡

፩. ንግስት የገዛችው ቀሚስ ያምራል፡፡
፪. የአንዳርጋቸው እናት ከገበያ ሽንኩርት፣ቃሪያና ቲማቲም ገዙ፡፡
፫. ሰዓዳ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ ናት፡፡
፬. ብርጭቆውን የሰበረው ልጅ በእናቱ ተገረፈ፡፡
፭. ከነቀምት የመጣው ሰውዬ ትናንት ወደ መቀሌ ተጓዘ፡፡
፮. ዕነኬብሮን ቆንጆ የሳሉን ውሻ አለቻቸው፡፡
፯. ሀና ያዘጋጀችው ምግብ በጣም ይጣፍጣል፡፡
፰. ሳሙኤል ከሁሉም ተማሪዎች አንደኛ በመውጣት የትምህርት ቤቱን ዋንጫ ወሰደ፡፡
፱. ሰለሞን ባረጋ የአስር ሺህ ሜትር የሩጫ ውድድር አሸነፈ፡፡

ገቢር፦ የተውኔት አንድ አብይ ክፍል ወይም ምዕራፍ ነው፡፡
መነባንብ/ንባበ አዕምሮ/፦ አንድ ገፀ ባህርይ ሌሎች ገጽ ባህሪያት በዙሪያው በለሌበት ቅፅበት የሚያስበውን
ሁሉ የሚያነበንብበት የብቻ ንግግር ነው
ጎንታ፦ አንድ ግፅ ባህርይ ሌሎች ገፀ ባህሪያት በዙሪያው ባሉበት ቅፅበትእነሱ እንዳይሰሙት ገለል ብሎ በራሱና በተደራሲያኑ የሚያነበንበው የብቻ ንግግር ነው፡፡
የተውኔት አላባውያን ፡- የተውኔት አላባዊያን የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው መድረክ(መቼት)፣ ጭብጥ፣ ተዋንያን (ገፀባህርይ)፣ ታሪክ፣ ትልም/ሴራ እና ቋንቋ ናቸው፡፡

ተግባር አራት፦

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

፩. ተዋንያን የሌሎችን ሰዎች ባህርይ ወርሰው ክዋኔን ከቋንቋ ጋር በማዋሀድ መድረክ ላይ የሚቀርብ የስነፅሁፍ ዘርፍ ምን ይባላል?

ሀ. ግጥም ለ. ተውኔት ሐ. ልቦለድ መ. ስነቃል

፪. ከሚከተሉት አንዱ የተውኔት ባህርይ አይደለም፡፡

ሀ. መድረክ ላይ ሲቀርብ በግልፅ የሚታይ ነው

ለ. ገፀባህርያቱ ምናባዊ ሳይሆኑ ገሀዳዊ ናቸው

ሐ. በተለያዩ ባለሙያዎች ትብብር የሚዘጋጅ ነው

መ. ገፀባህርያቱ ገሀዳዊ ሳይሆኑ ምናባዊ ናቸው

፫. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የተውኔት ሙያዊ ቃል አይደለም፡፡

ሀ. ትዕይንት ለ. ገቢር ሐ. ስንኝ መ. ቃለተውኔት

፬. ከተውኔት አላባውያን መካከል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ጭብጥ ለ. ገፀባህርይ ሐ. ቋንቋ

መ. መልስ አልተሰጠም

፭. -------------------------የተውኔት ገፀባህርያት ማቅረቢያ ዘዴ ነው፡፡

ሀ. ምልልስ ለ. ንግር ሐ. ምልሰት መ. ገለፃ

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

ተግባር፡-

፩. “ጠልፎ በኪሴ” የሚለውን ተውኔት ሀሳብ በመረዳት በሁለት
   አንቀፅ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

፪. አንድ የተውኔት ርዕስ መርጣችሁ አጭር ተውኔት በፅሁፍ አዘጋጁ፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

ዘይቤ

ዘይቤ የቋንቋ ለዛ ማለት ነው፡፡ለአገላለፃችን ጥንካሬ በመስጠት የምናስተላልፈው መልዕክት ጎልቶ ወይም ግልፅ ሆኖ እንዲታይ ለማድረግ የምንጠቀምበት አገላለጽ ወይም የአነጋገር ስልት ነው፡፡

የዘይቤ አይነቶች ብዙ ናቸው ዋና ዋናዎቹ ግን የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩. ተነፃፃሪ ዘይቤ
፪. ተለዋጭ ዘይቤ
፫. ሰውኛ ዘይቤ
፬. እንቶኔ ዘይቤ
፭. አያዎ ዘይቤ
፮. ምፀት ዘይቤ
፯. ግነት ዘይቤ

ተግባር፡-

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን የዘይቤ አይነቶች ፃፉ፡፡

፩. ----------------------------------የሰማይ ስባሪ የሚያክል ዳቦ ሰጠኝ፡፡

፪. ----------------------------------አጫውተኝ እንጅ ተራራው!

፫. ---------------------------------ህይዎት ያለው በድን

፬. ---------------------------------ብዕር አለቀሰ፡፡

፭. --------------------------------እጁ በረዶ ሆነ፡፡

፮. --------------------------------ሄለን እብድ ይመስል ጨርቋን ጣለች፡

